Bundesamt
für Migration
und Flüchtlinge

# በኢንተግሬሽን ትምህርት ኮርስ ለሚሳተፉ ግለሰቦች የተዘጋጀ፣ በአንቀጽ 13፣ 14 የዳታ ጥበቃ መሰረታዊ ደንብ (DSGVO) መሰረት የዳታ ሂደትን የሚገልጽ የመረጃ ጽሑፍ

የኢንተግሬሽን ኮርስ በኢሚግሬሽንና ስደተኞች ፌደራላዊ ጽሕፈት ቤት ተቀናጅቶ የሚከናወን ሲሆን፣ ለዚህ የግልና የመንግስት ትምህርት ሰጪ ድርጅቶችን ይጠቀማል፣ § 43 አዝባር 3 ዓረፍተ ነገር 2 የመኖሪያ ሕግ።

ይሄንን ሓላፊነት ለማሟላት ተብሎ የርስዎ የግል ዳታዎች በሚቀጥሉት ጽሕፈት ቤቶች ይመዘገባሉ እንደዚሁም በሂደት ውስጥ ይገባሉ:

- ፌደራላዊ ጽሕፈት ቤት ለሚቀጥሉት ዓላማዎች ኣስፈላጊ የሆኑትን የርስዎን የግል ዳታዎች መዝግቦ ያስቀምጣል:
    - በኣንድ የኢንተኢግሬሽን ትምህርት እንዲሳተፉ ለመፍቀድ (§ 5 አዝባር 1 የኢንተግሬሽን መምርያ) እንደዚሁም ቢበዛ እስከ 300 የትምህርት ሰዓታት የቋንቋ ትምህርት መድገምን ለመፍቀድ (§ 5 አዝባር 5 የኢንተግሬሽን መምርያ)
    - ከኢንተግሬሽን ትምህርት ክፍያ ነጻ ለማድረግ (§ 9 አዝባር 2 የኢንተግሬሽን መምርያ)
    - ለመጓጓዣ ክፍያ ድጎማ ለመፍቀድ (§ 4a አዝባር 1 የኢንተግሬሽን መምርያ)
    - ለኢንተግሬሽን ትምህርት ከሚከፈለው ክፍያ 50% ለማስመለስ (§ 9 አዝባር 6 የኢንተግሬሽን መምርያ)
- የውጭ ኣገር ተወላጆች ጽሕፈት ቤት፣ ለስራ ፈላጊዎች መተዳደሪያ የሚከፍሉ፣ በስደተኞች የክፍያ ሕግ መሰረት የሚከፍሉ ወይ ደግሞ የፌደራላዊ ኣስተዳደር ጽሕፈት ቤት ለርስዎ በትምህርት እንዲሳተፉ ፈቃድ ሲሰጡ ወይ ደግሞ እርስዎን ሲያስገድዱ፣ እነዚህ ጽሕፈት ቤቶች ለፌደራላዊ ጽሕፈት ቤት የርስዎን የግል ዳታዎች ይልካሉ፣ በተለይም የመሳተፍ ፈቃድ ማረጋገጫ ዳታዎችና ለፈተናና መመዝገቢያ የሚተላለፉ ዳታዎችን ይልካሉ። እነዚህ ዳታዎች ለፌደራላዊ ጽሕፈት ቤት የሚተላለፉት በተለይም ለኢንተግሬሽን ትምህርት ክፍያና ክንውን ኣስፈላጊ ሲሆኑ ነው (§ 88a አዝባር 1 ዓረፍተ ነገር 1 የመኖሪያ ሕግ)።
- ፌደራላዊ ጽሕፈት ቤት እርስዎን በ § 7 አዝባር 3 ወይም 5 የኢንተግሬሽን መምርያ መሰረት በኣጭር ጊዜ ውስጥ በትምህርት እንዲሳተፉ በኣንድ የትምህርት ሰጪ ድርጅት ከመደበዎት ወይም ወደ ኣንድ የትምህርት ሰጪ ድርጅት ከላከዎት፣ ፌደራላዊ ጽሕፈት ቤት ለትምህርት ሰጪ ድርጅቱ መረጃ ይሰጣል እንደዚሁም (እርስዎን የሚመለከት ከሆነ) እርስዎን በትምህርት እንዲሳተፉ ላስገደደ ኣካል መረጃ ይሰጣል።
- ስርዓቱን ጠብቀው ትምህርቱን እንደሚከታተሉ ለማረጋገጥ፣ ትምህርቱን ስኬታማ እንደሆነ ወይም ስኬታማ እንዳልሆነ የሚገልጽ የምስክር ወረቀት ለማተም ሲያስፈልግ ወይም ክፍያንና ክንውንን በሚመለከት ኣስፈላጊ ከሆነ፣ ትምህርት ሰጪ ድርጅቱ ለፌደራላዊ ጽሕፈት ቤት፣ ለኢንቴግሬሽን ትምህርት እንደተመዘገቡና በኢንቴግሬሽን ትምህርት እንደሚሳተፉ የሚገልጹ ዳታዎችን ይልካል (§ 88a አዝባር 1 ዓረፍተ ነገር 1 የመኖሪያ ሕግ)።
- በ § 4 a አዝባር 2 የኢንተግሬሽን መምርያ መሰረት የኢንተግሬሽን ትምህርቱን የሚያጅብ የልጆች እንክብካቤ የሚጠቀሙ ከሆነ፣ ትምህርት ሰጪ ድርጅቱ የሚንከባከባቸውን ልጆች ስም፣

KNr. 630.154b Amharisch BAMF 04/2024

መጠሪያ ስምና የልደት ዕለትን ይመዘግባል፣ ትምህርት ሰጪ ድርጅቱ ይሄንን መረጃ የሚሰበስበው በኢሚግሬሽንና ስደተኞች ፌደራላዊ ጽሕፈት ቤት ለማስፈቀድና ለዚሁም ደረሰኝ ለመጻፍ እንዲጠቅመው ተብሎ ነው።

- በኢንተግሬሽኑ ትምህርት እንዲሳተፉ የተገደዱ ከሆኑና ስርዓቱን ጠብቀው ትምህርቱን የማይከታተሉ ከሆኑ፣ ትምህርት ሰጪ ድርጅቱ፣ እርስዎን በዚህ ትምህርት እንዲሳተፉ ላስገደደ/ዱ አካል/ት መረጃ ይሰጣል (§ 88a አዝባር 1 ዓረፍተ ነገር 2 የመኖሪያ ሕግ)።
- የሚመለከተው የውጭ አገር ተወላጆች ጽሕፈት ቤት፣ ለስራ ፈላጊዎች መተዳደሪያ ለመክፈል የሚመለከተው አካል፣ በስደተኞች የክፍያ ሕግ መሰረት ክፍያ ለመክፈል የሚመለከተው አካል ካመለከቱ፣ በተለይም ማመልከቻው አንድ የመግቢያ ፈቃድ ለመስጠት፣ የኢንተግሬሽን ትምህርት ለመፍቀድ ወይ ደግሞ ለማስገደድ፣ የመሳተፍ ግዴታ መሟላቱን ለመቆጣጠር እንደዚሁም የመኖሪያ ፈቃድ ለማራዘም ተብሎ የቀረበ ከሆነ፣ ፌደራላዊ ጽሕፈት ቤት የርስዎን የግል ዳታዎችን ለነዚሁ አካላት ይልካል (§ 88a አዝባር 1 ዓረፍተ ነገር 3 የመኖሪያ ሕግ)።

ፌደራላዊ ጽሕፈት ቤቱ ራሱ የመዘገባቸውና ከሌሎች አካሎች የተቀበላቸውን የርስዎን የግል ዳታዎችን ለመጠበቅና ዋስትና የመስጠት ሓላፊነት አለበት።

የፌደራሉ ጽሕፈት ቤት አድራሻ:

Bundesamt für Migration und Flüchtlinge

Frankenstraße 210

90461 Nürnberg

በፌደራሉ ጽሕፈት ቤት ዳታዎችን ለመጠበቅ ሓላፊነት ያለው ክፍል አድራሻ:

Bundesamt für Migration und Flüchtlinge

\- Behördlicher Datenschutzbeauftragter -

Frankenstraße 210

90461 Nürnberg

የርስዎ ስም፣ ያባት ስምና የልደት ዕለት ቢዘገይ የኢንተግሬሽኑን ትምህርት ከጨረሱበት ጊዜ ጀምሮ ከአስር ዓመት በኋላ፣ የተቀሩት የግል ዳታዎች ደግሞ ቢዘገዩ ከአምስት ዓመት በኋላ ይሰረዛሉ (§ 8 አዝባር 6 የኢንተግሬሽን መምርያ)

በርስዎ የግል ዳታዎች የሚካሄደው ሂደት፣ ጥበቃ የሚያስፈልጋቸውን የርስዎን ወይ ደግሞ የሌላውን ዋስትና ፍላጎት የሚገድቡ እንደሆኑ ማሳመን ከቻሉ፣ የርስዎ የግል ዳታዎች በተገደበ ሁኔታ ሂደታቸው እንዲካሄድ፣ ለፌደራላዊ ጽሕፈት ቤት ማመልከቻ የማቅረብ መብት አለዎት። ከዚህ በኋላ ሂደቱ የሚካሄደው፣ ለሂደቱ የመንግስት ፍላጎት ከዚህ ያመዘነ ሲሆን ብቻ ነው። ከዚህ በተረፈም የርስዎ የግል ዳታዎችን የሚመለከት መረጃ የመጠየቅና የማረም መብት አለዎት እንደዚሁም በርስዎ ዳታዎች አለአግባብ የተካሄደ ሂደት ከኖረ፣ የማሰረዝ መብት አለዎት።

ከዚህ በተረፈም ዳታዎች ለመጠበቅ ሓላፊነት ላለው ተቆጣጣሪ ጽሕፈት ቤት አቤቱታ የማቅረብ መብት አለዎት:

Bundesbeauftragte für den Datenschutz und die Informationsfreiheit

Graurheindorfer Straße 153
53117 Bonn